# ቤተክርስቲያንህ ማደግ ትችላለች

## ለማንኛውም አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚሆን ራዕይ



የቤት ተልዕኮ



የአካባቢ ተልዕኮ



ዓለም አቀፍ ተልዕኮ

*“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ። ”* *የሐዋርያት ሥራ 1፥8*

| | |
|---|---|
| **የቤት ተልዕኮ** | **የእኛ እየሩሳሌም** |

**ቤተሰባችን እና ጓደኞቻችን**

---

| | |
|---|---|
| **የአካባቢ ተልእኮ** | **የኛ ይሁዳ እና ሰማርያ** |

**አካባቢያችን/ጎረቤቶቻችን**


---

| | |
|---|---|
| **የአለም አቀፍ ተልዕኮ** | **የምድር ዳርቻ** |

**መላው ዓለም**

---

# የቤት ተልዕኮ




እኛ እንደ መሐሏ ጠብታ ነን፤ በዙሪያችን ያሉት ጠብታዎች ደግሞ የእኛ ኢየሩሳሌም ናቸው።

**እያንዳንዱ አማኝ ወደ ኢየሩሳሌም (ቤተሰቡ፣ ጓደኞቹ እና የቅርብ ዘመዶቹ) የመድረስ ሃላፊነት አለበት።**

## ለቤተሰባችን መዳን መቆም እንዳለብን የሚነግሩን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ ማሳሰቢያዎች አሉ።

*“በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ ።” የሐዋርያት ሥራ 16፥31*

*“ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ ቤተሰቡን ለማዳን መርከብን በእምነት ሠራ ። ” ዕብራውያን 11፥7*

*“ለዘመዶቹ በተለይም ለገዛ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን **ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የከፋ ነው።”** 1ኛ ጢሞ 5፥8*

*“አባቴንና እናቴንም ወንድሞቼንና እኅቶቼንም ያላቸውንም ሁሉ እንድታድኑ፥ ሰውነታችንንም ከሞት እንድታድኑ።” ኢያሱ 2፥13*

*“ሰላዮቹም ብላቴናዎች ገብተው ረዓብን፥ አባትዋንና እናትዋን፥ ወንድሞችዋንም፥ ያላትንም ሁሉ፥ ቤተ ዘመዶችዋንም ሁሉ አወጡ፤ ከእስራኤልም ሰፈር በውጭ አስቀመጡአቸው።.... ኢያሪኮን ሊሰልሉ ኢያሱ የሰደዳቸውንም መልክተኞች ስለ ሸሸገች ጋለሞታይቱን ረዓብን፥ የአባትዋንም ቤተ ሰብ፥ ያላትንም ሁሉ ኢያሱ አዳናቸው፤ እርስዋም በእስራኤል መካከል እስከ ዛሬ ድረስ ተቀምጣለች።” ኢያሱ 6፥23-25*

# የአካባቢ (ሰፈር) ተልዕኮ



እያንዳንዱ አማኝ ለቤቱ ተልዕኮ ከተነቃቃ፣
የአካባቢ (ሰፈር) ተልዕኮ ቀላል ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ ተልዕኮ



ከዚያም ቤተክርስቲያን (የክርስቶስ አካል)
በዓለም ዙሪያ ያልተደረሱትን ለመድረስ ትችላለች።

# የቤት ተልዕኮ ስትራቴጂ

1. **የቤተክርስቲያን አመራር አካል ቁልፍ ነው።** የአመራሩ ተሳትፎ ከሌለ ራዕዩ ሊተገበር አይችልም።

   *"ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፥ እስከ አሮን ጢም፥*
   *በልብሱ መደረቢያ እንደሚወርድ ሽቱ ነው።" መዝሙረ ዳዊት 133÷2*

   *"በእስራኤል ውስጥ መሪዎች ስለ መሩ፥*
   *ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ስለ ሰጡ፥*
   *እግዚአብሔርን አመስግኑ።" መሳ. 5÷2*

2. ከአመራር አካሉ መካከል ቢያንስ ሁለት መሪዎች የራዕዩ ባለ አደራዎች ቢሆኑ ይመረጣል።

3. ለወንጌል ልብ ካላቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት (ከአመራር ውጪ)፣ ሁለት ወይም ሦስት፣ ከላይ ካሉት ሁለቱ የአመራር አካል ጋር በመተባበር የራዕዩ ባለ አደራዎች ይሆናሉ።

4. እነዚህ አራት ወይም አምስት የራዕዩ ባለ አደራዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህንን ራዕይ ለማመቻቸት አንገት በራስ እና በአካል መካከል እንደሚሄድ በአመራር አካል እና በጉባኤው መካከል ይሆናሉ።

5. የዚህን ራእይ አተገባበር እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለጉባኤያቸው በሚመች መልኩ መጠነኛ ማሻሻያ ማድረግ ይችላሉ።

## 1. ራዕዩ በአጥቢያ ቤ/ክ እንዲወለድ

### ግሎባል የምሥራች ሚሽን፣ የአጥቢያ ቤተክርስትያን አመራርን ሊረዳ ይችላል:-

- ራእዩ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዲወለድ ማድረግ
- ራእዩ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ እንዲሰርጽ ራእዩን ለጉባኤው ማስተላለፍ።
- ራእዩን በአማኞች መካከል መተግበር።
- ቀጣይ ሂደቱን መከታተል እና መገምገም።
- እንደ አስፈላጊነቱ ስልጠና መስጠት።

## 2. ትግበራ

- ምእመናን ራእዩ እንዲታያቸው መርዳት። “ራእይ ከሌለ ሕዝብ መረን ይሆናል” ምሳሌ 29፥18

- በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች በራሳቸው ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ስም በተዘጋጀው ቅጽ ላይ (በመጨረሻው ገጽ ይመልከቱ) እንዲሞሉ መርዳት።

- የተሞሉት ቅጾች ለጸሎትም ሆነ ለክትትል በሚያመች መልኩ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሥር ይያዛሉ።

- በቅጾቹ ላይ ላሉት፣ በእያንዳንዱ አማኝ ለሚወከሉት ለእነዚህ ነፍሳት በቤተ ክርስቲያን በኩል በትኩረት እንዲጸለይ ማድረግ። እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ በራሱ ዙሪያ ላሉት በቅጹ ላይ ላሰፈራቸው ነፍሳት ይጸልያል። የጸሎት አገልግሎት፣ የቤ/ክ አገልጋዮች፣ ወዘተ … ለእነዚህ ነፍሳት መጸለይ ላይ ያተኩራሉ።

## 3. ክትትል

- በእያንዳንዱ አማኝ የተጠቀሱትን ነፍሳት እንዴት በወንጌል መድረስ እንደሚቻል ስልት ማውጣት። አማኙ ግለሰብ በዋናነት በራሱ ዙሪያ ላሉት ኃላፊ ይሆናል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉት የዚህ ራዕይ ባለ አደራዎች በቅጾቹ ላይ ያሉትን ነፍሳት በተመለከተ ከግለሰቡ አማኝ ጋር በመመካከር ነፍሳቶችን ለመድረስ ልዩ ልዩ ስልቶችን ይነድፋሉ።

- መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራቸው፣ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም (በግል ምሥክርነት፣ በትራክት፣ በስልክ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ ለተዘረዘረው ሰው ቅርብ የሆኑ አማኞችን በመጠቀም ወዘተ …) ወንጌል እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ። *“ባልሰሙት እንዴት ያምናሉ?” ሮሜ. 10፥14*

- በቅጹ ላይ ላሉት ነፍሳት በአግባቡ ከተጸለየና በወንጌል ከተደረሱ ሁሉም ባይባል በከፊል የማይድኑበት ምክንያት ስለ ሌለ፣ ነፍሳቶች ጌታን ሲቀበሉ እና ሲድኑ፣ መላው ቤተ ክርስቲያን የደስታው ተካፋይ እንድትሆን እና እንድታመሰግን ክትትል ማድረግ።

# Global Good News Mission

## ኢየሩሳሌማችንን እንድረስ

### እያንዳንዱ አማኝ ለቤተሰቡና ለወዳጆቹ ኃላፊነት አለበት

**የቤተ ክርስቲያን ስም:** ______________________ **ቀን:** ____________

Full Name (ስም)፤ ______________________ Cell Phone (ስልክ ቁጥር)፤ ______________

EMAIL (ኢሜይል)፤ ______________________

Full Address (ሙሉ አድራሻ)፤ ______________________________________

**ወደ ጌታ እንዲመጡ በእምነት የምቆምላቸው የቅርብ ወገኖቼና ጓደኞቼ እነዚህ ናቸው፤ (Please write clearly)**

| | Name (ስም) | ዝምድና Relationship | Gender - ጾታ | | Age group (የዕድሜ ክልል) | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | M(ወ) | F(ሴ) | <20 | 20-34 | 35-49 | 50-70 | >70 | |
| 1 | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | |

ይህንን ከግቡ ለማድረስ ሥልጠና ያስፈልገኛል ☐




"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ; በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።

የሐዋርያት ሥራ 1÷8

## ግሎባል የምሥራች ሚሽን

**info@globalgoodnews.org**

WWW.GLOBALGOODNEWS.ORG

**www.facebook.com/GlobalGoodNewsMission**